# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ጥር 21 ቀን 2003 ዓ.ም.**

**-ወያኔ ደመወዝ ጭማሪ አደረግኩ ቢልም ለሹማምንቱ መሆኑ ተጋለጠ፤**

**-መከላከያና የፌዴራል ፖሊሶች በአለቆቻቸው ላይ ቁጣ ማንሳት ጀመሩ፤**

**በአዲስ አበባ ዜጎች እየታፈሱ መሆኑ ታወቀ፤**

ከአንድ ዓመት በላይ ፕሮፓጋንዳ ሲጎሰምለት እና ነጋሪት ሲመታለት የከረመው የደመወዝ ጭማሪ ሰሞኑን ተደረገ ተብሎ ይፋ ቢሆንም አሁንም ዝቅተኛውን ሰራተኛ ያላገናዘበና ጭራሽ የረሳ ብሎም የዘነጋ በአንጻሩ ደግሞ የወያኔ ድልብ ባለስልጣናትን ጥቅም ያስጠበቀ በመሆኑ ውስጥ ውስጡን ከፍተኛ ተቃውሞ እያስነሳ መሆኑ ታወቀ::

በ ተለያዩ ወቅቶች የክልል ፕርዝዳንትነት የውሀ ሀብት ሚኒስትርነ የቲክኖሎጂ ሚኒስትር ዛሬ ደግሞ ወርዶ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትር የሆነው የወያኔው ተላላኪ ጁኔዲ ሳዶ የሚመራው ኮሚተ ባቀረበው ጥናት መሠረት ወያኔ የደመወዝ ጭማሪ አደረግኩ ብሎ ይናገር እንጂ ከጥቅሙ ጉዳቱ

እንደሚያመዝንና ይህንኑ ድርጊት በመንቀፍ ሰራተኞች እና ሰራዊቱ በተቃውሞ ለመግለጽ እያቆበቆቡ መሆኑ ታውቆዋል::

በህዝብ ላብ እና ወዝ ቀድመው የጠገቡ የወያኔ ሹመኛ ካድሬዎችን ከመቼውም ግዜ በላይ ተጠቃሚ ያደረገው ይሄው ደመወዝ ጭማሪ የወያኔን ስልጣን ማራዘሚያ ስልት ሆነ እንጂ ዝቅተኛ የነበሩትን ሰራተኞች አሁንም በነበሩበት ችግር ውስጥ እንዲዳክሩ ከማድረግ ባለፈ አንዳችም ለውጥ እንደማያመጣላቸው በንዴት እየገለፁም ይገኛሉ::

ዝቅተኛውን ክፍል ተጠቃሚ ያደረገ ነው የተባለው ይሄው የደመወዝ ጭማሪ ቀድሞ 320 ብር ሲከፈላቸው የነበሩት ሰራተኞች አሁን 440 ብር እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን እስከ ዛሬ ከልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች ሌላ 4ሺህ ብር ሲከፈላቸው የነበሩት የወያኔ ሹማምንቶች ግን ወደ 5400 ብር እንዲያሻቅብላቸው መደረጉ አሁንም እነሱን ለመጥቀም የወጣ መመሪያ መሆኑ በግልፅ መረጋገጡ ታውቆዋል::

የነዳጅ ዋጋ በዓለም ላይ ተረጋግቶ እና ተመጣጣኝ ሆኖ በሚገኝበት በአሁኑ ወቅት ወያኔ የሚሉት ስግብግብ ቡድን በሀገሪቱ ህዝቦች ላይ ዋጋ እየቆለለ እሱን ተከትሎ የኑሮ ውድነቱ እየጦዘ በመጣበት በአሁኑ ሰዓት ለዝቅተኛው ሰራተኛ ህይወት መለወጫ ተብሎ ለዓመት ያህል ሲነገርለት የከረመው የደመወዝ ጭማሪ በ120 ብር ብቻ ቆሞ ለሹማምንቱ እና ለሚስቶቻቸው ግን ከ1500 ብር በላይ ጭማሪ መደረጉ በእጅጉ የሚያሳፍር እና ሀብታምና ደሀ በግልጽ የተለያዩባት ሀገር ለመሆን እየተገደደች እንደሆነ አመላካች ነው ተብሎዋል::

ለዝቅተኛው ሰራተኛ 39 በመቶ ጭማሪ አደረግኩኝ በማለት እንደትልቅ ነገር ሲነገርለት የከረመው ጭማሪ 320 ብር ሲከፈላቸው የነበሩት ሰራተኞች 440 ብር ብቻ እንዲያገኙ ሲደረግ የሻይ፣የቢሮ መጠበቂያ፣ የነዳጅ እና የሌሎች ወጪዎች ከሁለት እና ሶስት መመኪኖች በተጨማሪ ቋሚ ደመወዛቸው 4 ሺህ ብር እና ከዛም በላይ የሆኑ የወያኔ ካድሬዎች እና ሹምንቶች ግን 38 በመቶ ተጨማሪ ተደርጎላቸው በአንድ ግዜ የ1520 ብር ጭማሪ እንደተደረገላቸውና ልዩነቱ እጅግ የሰፋ መሆኑን ሰራተኞች በምሬት እየገለፁ ይገኛሉ::

ለሰራተኛው ተቆርቋሪ እና አሳቢ በመምሰል ሲወተውት የከረመው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ጭማሪው እጅግ ስር ነቀል ለውጥ እንደሚያመጣ በተደጋጋሚ በምክር ቤት ውስጥ ጭምር ሲወተውት የነበረ ቢሆንም እንደተናገረው ለበታች ሰራተኞች እና ለመሀከለኛው ሳይሆን ቀድሞም በህዝብ ሀብት የጠገቡትን እና የደለበ ደመወዝ ያላቸውን ሹመኞች ከተቀረው ሰራተኛ ጋር እንዳይቀራረብ ያደረገ መሆኑ በይፋ ታውቆዋል::

አስገራሚው እና አስቂኙ ነገር ያለ አንዳች ስራ ተወዝፈው እጅ ሲያወጡና ሲያወርዱ ለሚውሉት የምክር ቤት አባሎች የህዝብ ተመራጭ በመሆናቸው 35 በመቶ ተጨምሮላቸዋል በማለት ይፋ ያደረገው ጁኔዲ ሳዶ እነዚህ ግለሰቦች ደመወዛቸው 3500 ብር በመሆኑ አሁን ተደረገ የተባለው ጭማሪ ሲሰላ 1225 ብር ጭማሪ እንደተደረገላቸውና በቀጥታ ከሌሎች ጥቅማጥቅሞች በተጨማሪ 4725 ብር ደመወዝ እንዲከፈላቸው ተደርጎዋል::

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እና በሌሎች ዩኒቨርስቲ ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራኖች ከዚህ ቀደም ስለ ደመወዝ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር ውይይት አድርገው የ105 በመቶ ጭማሪ እንደሚደረግላቸው የተስማሙ ቢሆንም አሁን ሰሞኑን ተደረገ በተባለው ጭማሪ ግን ቃል የተገባላቸው ተፈጻሚ ባለመሆኑ ከፍተኛ ተቃውሞ እያቀረቡ መሆኑም ታውቆዋል::

ችሎታ የሌላቸውና ያለ አንዳች ስራ በየቢሮው ተወዝፈው ለሚቀመጡ የወያኔ ባለስልጣናት ደመወዛቸውን እየቆለሉ መሸከም ከሚችሉት በላይ እየጫኑላቸው ለመምህራን ግን ለመጨመር ፈራ ተባ እያሉ በመገኘታቸው ሰሞኑን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እንዲሁም በሌሎችም ካምፓሶች እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራኑ ጥያቄ በማንሳት ላይ እንደሚገኙ ታውቆዋል::

የደመወዝ ጭማሪው የኑሮ ማካካሻ ይሆናል ብሎ መለስ ዜናዊና ቡድኑ እየተቀባበሉ ሲያናፍሱ የከረሙ ቢሆንም የኑሮው ውድነት ከሚፈለገው በላይ ፈጣን እድገት እያስመዘገበ በመምጣቱ ሰራተኛው ከፍተኛ ችግር ውስጥ ወድቆ እንደሚገኝ እያወቁ እዚህ ግባ የሚባል ጭማሪ ሳይደረግ መቅረቱ በመከላከያ፤ በፖሊስ እና በሌሎችም መንግስታዊ መስሪያ ቤት ውስጥ ያሉ ሰራተኞች ተቃውሞ ለማንሳት እያጉረመረሙ መሆኑ ታውቆዋል::

ወያኔ በሀገሪቱ ውስጥ የተፈጠረውን የኑሮ ውድነት በብዙ መልኩ ድጎማ አድርጎ ማስተካከል ሲገባው ጥፋቱን በህዝቡና በነጋዴው ላይ ለጥፎ ነጻ ለመሆን ቢሞክርም ችግሩ እየሰፋ እና እየገዘፈ በመምጣቱ ሊወጣው ከማይችለው አዘቅት ውስጥ እየተዘፈቀ መሆኑን የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ይናገራሉ::

ወያኔ 1ሚሊዮን ለሚሆኑ የመንግስት ሰራተኞች የደመወዝ ጭማሪ አደረግኩኝ እያለ ቢያቅራራም ገበሬውን ጨምሮ ሌሎች የሀገሪቱ 80 ሚሊዮን ህዝብ የሚያገኘው ድጎማ ወይም ገቢ ስለሌለው ችግሩ የከፋ ሁኔታ እንደሚሆን እየተነገረ ሲሆን ገበሬውም በማዳበሪያና በሌሎች ግብዓቶች ላይ የሚያገኘው ድጎማ ባለመኖሩ በሚያመርተው ምርቶች ላይ ጭማሪ ማድረግ ግድ የሚለው በመሆኑ በቅርቡ የእህል ዋጋ ሊንር እንደሚችል ስጋታቸውን የሚገልጹ የከተማ ነዋሪዎች በርካቶች ናቸው::

የግል ድርጅት ሰራተኞች እና በቀን ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ዜጎችም በበኩላቸው መጪው ግዜ ጨለማ እንደሆነባቸውና ኑሮን መቋቋቋም እንደማይችሉ ገልጸው መፍትሔው በቱኒዚያ፤ በግብፅ እንዲሁም በየመን እንደተቀጣጠለው የህዝብ አመጽ እኛም በወያኔ ላይ መጀመር ብቻ ነው ሲሉም በንዴት እየገለጹ ናቸው::

እስከ ዛሬ ወያኔ ህዝብን ለማፈኛ ሲጠቀምባቸው የነበረው የመከላከያ ሰራዊት አባሎች እና የፌዴራል ፖሊሶች ጭምር በተደረገው ጭማሪ እጅግ ከማዘናቸውም በላይ የተከፉ በመሆኑ ሰሞኑን ሁሉም በየጦር ክፍሉና በየካምፑ በቅርብ አለቆቻቸው ላይ ቁጣቸውን እያሰሙ ከመሆኑም በተጨማሪ የጠየቅነው ጥያቄ ምላሹ በአስቸኩዋይ እንዲመጣልን ሲሉም ቁጣ አዘል መልዕክት እያስተላለፉ መሆኑን የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

በህዝብ እና በሀገር ላይ እየተጫወተና እየቀለደ የሚገኘው ወያኔ ለይምሰል ጭማሪ አደረግኩኝ እያለ ጢባጢቤ ሲጫወት እና በሰራተኞች ህይወት ሲቀልድ አልፎ ተርፎ የመከላከያና የፌዴራል ፖሊስ ኃይሎች ቁጣ ለመግለጽ በተዘጋጁበት በአሁኑ ግዜ የተቃዋሚ መሪ ነን የሚሉት ግለሰቦች የህዝቡን

አመጽ ውስጥ ውስጡንም ሆነ በግልፅ ከማስተባበር ይልቅ ወደ ሁዋላ እያፈገፈጉ መገኘታቸው በእጅጉ የሚያሳፍር መሆኑን ህዝቡ በምሬት እየተናገረ እንደሚገኝ ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል::

የፌዴራል ፖሊስ እና የአዲስ አበባ ፖሊስ አባሎች በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በተለይ ሐሙስ እና ዓርብ ዕለት በየፊናቸው በብስጭት ገሚሱ በመሸታ ቤት ገሚሱ ስራ አንገባም በማለት ህዝብ እየሰማቸውና እያያቸው የተደረገላቸውን የደመወዝ ጭማሪ በአደባባይ ሲያወግዙ በአንጻሩ ለአለቆቻቸው የተደረገው ጭማሪ እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ ሲነቅፉና አንዳንዶቹ በተለይ ከበረሀ መጥታችሁ ሳትማሩ አለቃ አደረጉዋችሁ አሁን እኛ ባርያ እናንተ ጌታ ሆናችሁ እስከ ማለት የተደረሰበት እና በቃላት አለቆቻቸውን እየሞለጩ የሚገኙበት ወቅት ላይ መደረሱ ታውቆዋል::

የኑሮ ውድነቱ እንዲረግብ ከማድረግ ይልቅ እንዲከርር......የጋለው ገበያ እንዲበርድ ከማድረግ ይልቅ እንዲባባስ እያደረገ ያለው ዘረኛው እና አምባገነኑ የወያኔ ቡድን የአንድ ኪሎ ስኩዋር ዋጋ ከፋብሪካ 3 ብር ከ50 ሳንቲም አውጥቶ ለነጋዴ 13ብር ከ80 መሸጡ ብሎም በማዳበሪያ ላይ ስንጥቅ ትርፍ ለማግኘት በገበሬው ላይ የቆለለው ዋጋ እንዲሁም በነዳጅ ላይ ያደረገው ጭማሪን ተከትሎ በተፈጠረው ችግር ቅንጣት ታክል እፍረት ሳይሰማው በማን አለብኝነት ስሜት ተወጥሮ አሁን ያለበት ችግር እንዲደርስ ያደረገ ከመሆኑም በላይ ማስመሰያ የደመወዝ ጭማሪ አደረግኩኝ ቢልም አሁንም ችግሩ ስር እየሰደደ እና ወደ ከፋ ሁኔታ እየገፋ መጣ እንጂ አንዳችም ያመጣ ለውጥ እንደሌለ ታውቆዋል::

በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት እንዲሉ የወያኔ ቱባ ባለስልጣናት እና በየወረዳውና ቀበሌው ተሾመው የተቀመጡ የአዲሱ ደመወዝ ጭማሪ ዋነኛ ተጠቃሚዎች በቴሌቪዥን እየቀረቡ መግለጫ እንዲሰጡ በታዘዙት መሰረት የተደረገውን የደመወዝ ጭማሪ እያደነቁና እያወድሱ ቢሆንም አሁን በሀገሪቱ ያለው ተጨባጭ እውነታ ግን እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ከመድረሱም በላይ ከገጠር እስከ ከተማ.....ከሰራተኛ እስከ መምህራን.....ከመከላከያ እስከ ፌዴራል ፖሊስ ድረስ ሁሉም በየፊናው ውስጥ ውስጡን ተቃውሞ እያሰማ መሆኑ ታውቆዋል::

በወያኔ ሹማምንቶች እስከ ዛሬ ድረስ እንደ ጋሪ ፈረስ ግራና ቀኙን እንዳያይ ተደርጎ የተቀመጠው የመከላከያ ሰራዊት ዛሬ በራሱና በቤተሰቦቹ ውስጥ ሰርስሮ ዘልቆ የገባው የኑሮ ውድነት ችግር ከእግር ጥፍሩ እስከ ራስ ፀጉሩ ድረስ በመድረሱ መሸከም ከሚችለው በላይ በመሆኑ በአለቆቹ ላይ እያፈጠጠ እና እያጉረጠረጠ በመሆኑ የቅርብ አለቆች የተባሉት የኮሎኔል ማዕረግ ያላቸው መኮንኖች በፍርሀት ተውጠው ለበላይ አለቆች ሪፖርት እያቀረቡ እንደሚገኙ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የደረሱን ጥቆማዎች አስረድተዋል::

ህዝብ በኑሮ ውድነቱ እየተጠበሰ በችግሩ እየተቆላ ባለበት በአሁኑ ሰዓት የወያኔ ቡድን በህዝቡ ገንዘብ የመከላከያና የፌዴራል ፖሊስ ብሎም የማረሚያ ቤት ሹማምንቶችን ወደ ውጭ ሀገር እየላከ እያዝናና መሆኑ ስርዓቱ እየበሰበሰና እየዘቀጠ መምጣቱን የሚያሳይ ነው ያሉት የፌዴራል ፖሊስ አባሎች በተለይ ደመወዝ ጭማሪ ብለው በእኛ ላይ ማሾፋቸው ንቀውን እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል እያሉ ዛቻ ጭምር እየሰነዘሩ ይገኛሉ::

ይሄንኑ የመከላከያና የፌዴራል ፖሊስ አባሎች ጥያቄን ተከትሎ አርብ ጥር 20 ቀን 2003 ዓ.ም የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት በምስጢር ተሰብስበው አዲስ መመሪያና ድጎማ እንዲደረግላቸው የሚል ትዕዛዝ እንዲተላለፍ መደረጉን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሏል።

የተደረገልን ጭማሪ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም በእኛ ስም እየተነገደ ነው እያሉ ሰራዊቱም ሆነ የፌዴራል ፖሊስ አባሎች ሁሉም በየበኩላቸው ባቀረቡት ጥያቄና ባሰሙት ተቃውሞ የተደናገጡት የወያኔ ሹመኛ ካድሬዎች ድንገት ባደረጉት አስቸኳዋይ ስብሰባ ጭማሪው በተለየ ሁኔታ እንዲታይ እና እንዲፈጸም በሚል ስምምነት ተደርጎ እንደተወሰነላቸው ታውቆዋል።

መለስ ዜናዊ ኔዘርላንድ ለስብሰባ ቢሄድም ሁኔታው አሳሳቢ መሆኑን ባለበት ተነግሮት አስቸኳዋይ ማሻሻያ እንዲደረግላቸው እሱም የተስማማ ከመሆኑም በተጨማሪ በቱኒዚያና በሌሎችም ሀገራት የተጀመረው የህዝባዊ አመጽ እንዳይነሳ በመስጋት ሳይወዱ በግድ ጭማሪ ለማድረግ የተገደዱ መሆኑን ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል።

በዚሁ ለመከላከያ እና ለፌዴራል ፖሊስ አባሎች አደረግን ባሉት ማስተካከያ ላይ ምን ያህል ጭማሪ እንደሚደረግ በግልጽ ባይታወቅም ደመወዝ ሳይሆን ወያኔ ደስ ባለው ግዜና ባመቸው ወቅት ሊሰርዛቸው የሚችሉ መስፈርቶችን አዘጋጅቶ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ የቀለብ፣የልብስ፣የልጆች አበል በሚል ሰራዊቱን ለማጃጃል በሚያመቸው መልኩ ጭማሪ እንዲደረግ መወሰኑን አጋልጠዋል።

የሰራዊቱ አባሎች በንዴት የወያኔን ቡድን በግልጽ በአደባባይ እያወገዙ ቁጣቸውን ከመግለፃቸውም በተጨማሪ የቅርብ አለቆቻቸውን አፋጥጠው በመያዛቸው የተደናገጡት የወያኔ ሹመኛ ግለሰቦች አስቸኳዋይ ስብሰባ አድርገው የቀለብ፣የልብስ፣የልጆች አበል ይከፈላቸው ብለው ይወስኑ እንጂ ስንትና ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ በግልጽ ያልታወቀ መሆኑንም የደረሰን ጥቆማ ጨምሮ አብራርቶዋል።

የአፍሪካ የመሪዎች ስብሰባ ሊደረግ ጥቂት ቀናት ቀርቶት በነበረበት ወቅት የተደረገው ጭማሪ ላይ ሰራተኛውም ሆነ ሰራዊቱ ማጉረምረም በመጀመራቸው የተደናገጠው የወያኔ ቡድን በፍጥነት የሰራዊቱን ጥያቄ በማይሆን መልክ ለማዳፈን የወሰዱት እርምጃ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ አሁንም ጥያቄው ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚችል በወያኔ ባለስልጣናት ዘንድ ከወዲሁ ስጋት እንዳሳደረ ለመረዳት ተችሎዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በአዲስ አበባ የአፍሪካ የመሪዎች ስብሰባ ሊደረግ መሆኑን ተከትሎ ጥበቃውና ውጠራው እጅግ ከመጠናከሩም በተጨማሪ በየቦታው ድንገተኛ ፍተሻ እየተባለ ህዝቡ መከራውን እያየ መሆኑ ታወቀ።

ከሐሙስ ጥር 19 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከፍተኛ ውጥረት ከመኖሩም በላይ የደህንነት ኃይሎች በየመንደሩና በየሰፈሩ ተሰግስገው ህዝቡን ከማጨናነቃቸውም በተጨማሪ የሱማሌ ተናጋሪ ዜጎች እየታፈሱ እንደሆነ ለማየት ተችሎዋል።

አልሻባብ የተባለው አሸባሪ ቡድን ጥቃት ሊያደርስ ይችላል የሚል መረጃ ለብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቢሮ ስለደረሰ በአዲስ አበባ ከተማ ያሉ የሱማሌ ተወላጆች በሙሉ ከያሉበት

እየተለቀሙ ለእስር እንዲዳረጉ የሚል በደህንነቱ ባለስልጣን በጌታቸው አሰፋ ትዕዛዝ በመሰጠቱ በሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች እየተለቀሙ ለእስር እየተዳረጉ እንደሚገኙ ታውቆዋል፡፡

በዚህም መሰረት በቦሌ ፣በመገናኛ፣ በሳሪስ እና በተለያዩ ቦታዎች በሰላማዊ ኑሮ ላይ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሱማሌዎችን ከየመንገዱ ላይ እያፈሱ ለእስር ከመዳረጋቸውም በላይ ህጻናት ልጆቻቸውን ጭምር ቤት ጥለው የወጡ እናቶች ታፍሰው እየተጋዙ መሆኑ ታውቆዋል፡፡

እሁድ ጥር 22 ቀን 2003 ዓ.ም ይጀመራል የተባለው የአፍሪካ መሪዎች ስብሰባን ተከትሎ በሀገሪቱ ከፍተኛ ውጥረት ከመፈጠሩም በላይ ጠይም መልክ ያለውና አፉ የተኮላተፈ ዜጋ በሙሉ ያለ ምንም ማንገራገር እየታፈሰ እየተጋዘ ሲሆን ለግዜው ከአዲስ አበባ ውጭ እንደታሰሩ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

እስከ አሁን በአስር ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች ታፍሰው እየተጋዙ መሆኑን የአይን እማኞች የገለፁ ሲሆን ጥቃቱን ሊያደርስ ይችላል የሚል መረጃ ደረሰን ያለው የወያኔ የደህንነት ባለስልጣኑ ከሱማሌ የሚነሳ የአልሻባብ አክራሪ ቡድን ነው የሚል ወሬ እያናፈሰ መሆኑንም ጨምሮ የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

ወያኔ የውስጥ ችግሩን እና የፖለቲካ ግለቱን ለማብረድ ሲልና የባእዳንን ተልእኮ ለማሟላት ከኢትዮጵያ ህዝብ ይሁንታ ውጭ ጦሩን ወደ ሱማሌ አዝምቶ በሺህዎች የሚቆጠሩትን አስጨርሶ የተመለሰ ከመሆኑም በላይ ለኢትዮጵያና ለህዝቡዋ ዘላቂ የጎረቤት ጠላት እንድታፈራ ያደረገ መሆኑ የሚዘነጋ አይደለም፡፡

## ወ/ት ብርቱንን ተፈታች ሕዝብ የጋለ አቀባበል አደርጎላታል

## የወያኔው መሪ መለስ ከደኢህዴን ካድሬዎች ጋር የጠበቀ ፍቅር መጀመሩ ታወቀ፤

በወያኔ የግፍ እስር ቤት ስትሰቃይ የቆየችው የአንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ረቡዕ መስከረም 26 ቀን 2003 ዓም ከ18 ወራት እስራት በሁዋላ ተፈትታለች:: ከዚህ በፊት ከእስር ስፈታ መንግስትን ይቅርታ አልጠየኩም ብለሽ ለደጋፊዎችሽ ተናግረሻል በሚል ክስ ላለፉት 18 ወራት በእስር ስትማቅቅ የነበረችው ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ረቡዕ ዕለት 5 ሰዓት ላይ ከቃሊቲ እስር ቤት በእስር ቤት ተፈትታ ከእናትዋ እና ከህፃን ልጅዋ ጋር በመሆን ነበር ወደ ቤትዋ ለመግባት ችላለች:: ወደ ቤትዋ ስትገባ ከመኖሪያ ቤትዋ አከባቢ ከመንገድ ግራና ቀኝ በመሆን ሲጠባበቃት የነበረው በርከታ ሕዝብ የጋለ አቀባበል አድርጎላታል::

በሌላ በኩል የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ከበረሀ የመጡትን ቀስ በቀስ እያራገፈ ጥሎ የከተማ ጮሌዎችን ብቻ ሰብስቦ አዲስ ካቢኔ መመስረቱን ሰሞኑን ይፋ አድርጎዋል::በተለይ በትግል ላይ አብረን ነበርን ያላቸውን የህወሀት እና የብአዴንን ሰዎች አሽቀንጥሮ ጥሎ ትኩስ ፍቅር ከያዘው ከደኢህዴን ካድሬዎች ጋር አዲስ መንግስት መመስረቱን በይፋ ገልፆዋል::

ሰሞኑን መሰረትኩ ባለው አዲስ የመንግስት ካቢኔ ስልጣኑን ሙሉ ለሙሉ የያዘው እራሱ መለስ ዜናዊ ቢሆንም በተዋረድ ግን የደቡቡ ተወላጅ የደኢህዴኑ ሊቀመንበር እና አዲሱ ለገሰን ፈንግሎ የወያኔ ምክትል ሊቀመንበር የሆነው ኃይለማሪያም ደሳለኝ መሆኑም ታውቆዋል::

በህወሀት ክፍፍል ወቅት ተራ አባል የነበረና አባተ ኪሾ ከአንጃው ጋር ወግነሀል ተብሎ ወደ ዘብጥያ በወረደበት ወቅት ድንገት ሳይታሰብ ከየት መጣ ሳይባል ለጊዜው ማስታገሻ ይሆነኛል ብሎ የክልሉ ፕሬዝዳንት አድርጎ የሾመው እንደነበር ያስታወሰው ዘገባው ከዚያን ግዜ ጀምሮ ለመለስ በሚያሳየው ታማኝነት እና እንደ ፈጣሪው እያየ የሚርበተበት በመሆኑ አሁን ላለበት ስልጣን እንዳበቃው ለማረጋገጥ ተችሎዋል::

የአዋሳ ዩኒቨርስቲ ተራ መምህር በነበረበት ወቅት የወያኔ አባል በመሆን በጥቂት ዓመታት ውስጥ የዩኒቨርስቲው ፕሬዝዳንት ተደርጎ የተሾመ ሲሆን በዚያን ግዜ ተማሪዎች የሚያነሱትን ጥያቄ እያዳፈነነ በግድ እና በጡንቻ እያሳመነ የወያኔን የግፍ በትር የዘረጋ በመሆኑ በመለስ አይን ውስጥ ሊገባ

ቻለ ያሉት አብሮ አደጎቹ በተፈጠረው ክፍፍል ወቅትም የደቡብ ክልል ፕሬዝዳንት እና የደኢህዴን ሊቀመንበር ሆኖ እንደተሾመም አስታውሰዋል።

በ1994ዓ.ም ወደ ስልጣን በመጣ ግዜ ከበረሀ ከወያኔ ጋር  አብሮ የመጣው ፀጋዬ መሞ የተባለ ግለሰብ ምክትል ሊቀመንበር በመሆን አብሮ እየሰራ የነበረ ቢሆንም ኃይለማሪያም ስለዚህ ግለሰብ መጥፎነት ለመለስ ሹክ በማለቱ ግዜው ሳይደርስ ከስልጣኑ እንዳባረረውና እራሱ በእጩነት ያቀረበው ሽፈራው ሽጉጤ እንዲሾም ማድረጉንም አብራርተዋል።

በሀገሪቱ ከመለስ ቀጥሎ ቁልፍ ስልጣን የተሰጠው ይሄው የወያኔ አጨብጫቢ ግለሰብ አዋሳ በነበረበት ወቅት የሲዳማ ተወላጆች እትብታችን የተቀበረበት ቦታ ለማንም መጤ እየተሸነሸነ በመሆኑ ሊቆም ይገባል ቅድሚያ ለእኛ ይሰጠን በማለት የወያኔን ካድሬዎች በመቃወም የኢትዮጵያን ባንዲራና የኮባ ቅጠል እንዲሁም የዘንባባ ቅጠል ይዘው ሎቄ ከምትባል ከአዋሳ 16 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ተነስተው ወደ አዋሳ በመጉዋዝ ላይ እንዳሉ ለወያኔ አግአዚ ጦር ትዕዛዝ በመስጠቱ 46 ሰዎች ወዲያውኑ ሲገደሉ ከ100 በላይ የሚሆኑት ደግሞ ወደ ሆስፒታል ተወስደው እንደነበር ዘገባው አስታውሶዋል።

ይህንን የመሰለ  አረመኔ ተግባር የፈፀመ ግለሰብ ለእስር እና ለፍርድ መቅረብ ሲገባው ለመለስ ዜናዊ እንደራሴ ሆኖ በመስራቱ ብቻ በእድገት ላይ እድገት ተሰጥቶት የመለስ አማካሪ ሆኖ ወደ አዲስ አበባ እንዲዛወር  ተደርጎዋል።

ቀድሞ የነበሩትን የመለስ ጉዋደኞች በጥቂት ዓመታት ገልብጦ ለዚህ ስልጣን የበቃው ኃይለማርያም የመለስን ወሬ ወዳድነት በማወቁ ያልሆነውንና የሆነውን እየቀባጠረ በመያዙ ዛሬ ለከፍተኛ ስልጣን የበቃ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎች በደቡብ ተወላጆች እጅ መግባቱንም ዘገባው አስረድቶዋል።

ታናሽ ወንድሙን የዲላ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት አድርጎ የሾመው ኃይለማሪያም ደሳለኝ ሚስቱንም እዚሁ አዲስ አበባ ላይ ከፍተኛ ስልጣን ሰጥቶዋት እያሰራች መሆኑንም የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ገልፆ በተቃራኒው ግን ብዙ ምሁራኖችን አባል ሁኑ ሲል እምቢ በማለታቸው ብቻ ከዩኒቨርስቲ እያባረራቸው እንደነበር አጋልጠዋል።

መለስ ዜናዊ ከደኢህዴን ካድሬዎች ጋር እፍ ንፍስ ያለ ፍቅር ውስጥ ከመግባቱም በተጨማሪ ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን ሰጥቶ በታማኝነት እና በቅን ባርነት ይታዘዙኛል በሚል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፣ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፣ የመከላከያ ሚኒስትር ፣የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትርነቱንና ሌሎቹንም ቁልፍ ቦታዎች አስረክቦዋቸዋል።

የወያኔው መሪ መለስ ሰሞኑን ከሾማቸው 20 ሚኒስትሮች መሀከል ዋና ዋና የተባለውን ቦታ ከራሱ ቀጥሎ ለደኢህዴን ካድሬዎች አስረከበ የተባለ ቢሆንም ከውስጥ በኩል ግን ትልቅ ማነቆ የሚሰራለትን በረከት ስምኦንን በሚኒስርት ማዕረግ የመንግስት ኮሚኒኬሽን ተጠሪ አድርጎ እንዳስቀመጠባቸውም ለማወቅ ተችሎዋል።

ከ20 ሚኒስትሮች መሀከል 5 -ደኢህዴን ፤ 4 ብአዴን ፤ 5 ኦህዴድ፤ 2 የህወሀት፤ 2 የወያኔ ተለጣፊ የሆነው ሶህዴፓ ፤ 1 የወያኔ ተለጣፊ የሆነው አፋር እና 1 በግል የፓርቲ አባል ያልሆነ ተብሎ መሾማቸው ታውቆዋል::

ከ20ዎቹ ሚኒስትሮች በተጨማሪ በሚኒስትር ማዕረግ ሌሎች ሶስት የተሾሙ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ሁለት ከብአዴን አንድ ከኦህዴድ መሆኑንም ለማወቅ ተችሎዋል:: በሚኒስርት ማዕረግ የተሾሙት እና የሚኒስትሮች ካቢኔ አባል የሆኑት በረከት ስምኦን የመንግስት ኮሚኒኬሽን ተጠሪ፤መላኩ ፈንታ የገቢዎች ኤጀንሲ ኃላፊ እና አስቴር ማሞ ቀድሞ የወጣቶች እና ስፖርት ሚኒስትር የነበረችው የወያኔ የምክር ቤት ተጠሪ በመሆን ተሹመዋል::

**አምስቱ የደቡብ ተወላጅ ተሹዋሚዎች**

*1ኛ- ኃይለማሪያም ደሳለኝ -የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር*

(የወላይታ ብሄር ተወላጅ የደኢህዴን ሊቀመንበር እና የኢህአዴግ ምክትል ሊቀመንበር)

*2ኛ- ሲራጅ ፈርጌሳ -መከላከያ ሚኒስትር*

(የጉራጌ ብሔር ተወላጅ የደኢህዴን ስራ አስፈጻሚ እና ለኮታ ማሙያ ተብሎ ከክልል ተመርጦ የመጣው ባለፈው አመት የነበረ ሲሆን አሁንም በያዘው ቦታ እንዲቀጥል ተደርጎዋል::)

*3ኛ -ዶ/ር ሽፈራው ተክለማሪያም -የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር*

(የደኢህዴን ስራ አስፈጻሚ የወላይታ ብሔር ተወላጅ የደቡብ ክልል የጤና ቢሮ የነበረና በኃይለማርያም ምትክ የክልሉን ስልጣን ይረከባል ተብሎ ከፍተኛ ግምት ሲሰጠው የነበረ ቢሆንም ያልተሳካለት መሆኑን የጠቀሱት ምንጮቹ በ1998 ዓ.ም ጀምሮ በኮታ ማሙያነት የመከላከያ ሚኒስትር እንዲሆን ተቀምጦ የነበር::

*4ኛ ደሴ ዳልኬ -ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር*

ይህ ግለሰብ በኃይለማርያም አቅራቢነት በመለስ ዜናዊ አጽዳቂነት የመጣ ሲሆን ግለሰቡ የሲዳማ ዞን ዋና አስተዳዳሪ ሆኖ እየሰራ የነበረና በህዝብ ላይ ከፍተኛ ችግር የፈጠረ:: በተለይ ሎቄ ላይ ህዝቡ እንደ ቅጠል በአልሞ ተኩዋሽ ቅልብ የወያኔ ጦር ሲታጨድ ከሰራዊቱ ጋር ግንኙነት ፈጥሮ የነበረ ሲሆን ለዚሁ ለዋለው ውለታ የተሾመ መሆኑን ምንጮቹ አስረድተዋል::

*5ኛ- መኩሪያ ኃይሌ - የከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሚኒስትር*

ግለሰቡ የጉራጌ ብሔር ተወላጅ ሲሆን ዲላ ተወልዶ ያደገ በህዝብ ላይ የወያኔ ቡድን የሚጭነውን የግፍ ቀንበር አስፈጻሚ ሆኖ ሲሰራ ህዝቡ ሊገድለው ሲል አምልጦ የወጣ ከመሆኑም ባሻገር በአጭር ግዜ ውስጥ የአዲስ አበባ ከተማ ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ የነበረ መሆኑንና አሁን ደግሞ የካሱ ኢላላን ቦታ ሹመት የተረከበ ነው::

ከአዲሱ ሹመት ውስጥ ያልተካተቱና በጡረታ ስም የተወገዱት የወያኔ ባለስልጣናት

**1-ስዩም መስፍን -የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር**

**2-አዲሱ ለገሰ -ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር**

**3-ተፈራ ዋልዋ -የአቅም ግንባታ ሚኒስትር**

**4-ግርማ ብሩ -የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር**

**5-መሀመድ ድሪር -የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር**

**6 -ተሾመ ቶጋ -የህዝብ ተወካዮች አፈ ጉባዔ**

**7-አስፋው ዴንጋሞ -የውሀ ሀብት ሚኒስትር**

**8-ደግፌ ቡላ -የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤ**

**9 ካሱ ኢላላ -የስራና ከተማ ልማት ሚኒስትር እና ሌሎችም ናቸው።**